
# <u>እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2018 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

ባለፈው የጁላይ የመጀመሪያው አሥር ቀናት የወቅቱ የክረምት ዝናብ ከአመቺ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ጋር ተያይዞ በአብዛኛው በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ሥፍራዎች ላይ የቀጠለ ሲሆን፤ አልፎ አልፎም ከተጠናከሩ የደመና ክምችቶችም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደተመዘገበ የዝናብ መረጃዎች ያሳያሉ። ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች ውስጥ ለመጥቀስ ያህል አለም ከተማ 53.3 አይራ 37.2 አርጆ 38.4 ባቲ 38.0 ቻግኒ 50.3 ጨፋ 31.5 ዳንግላ 33.4 ደባርቅ 32.0 ፍቼ 40.3 ጊምቢ 63.7 ጎንደር 52.7 36.5 ጎሬ 65.8 ካቺሴ 44.5 44.0 40.6 30.9 መሀልሜዳ 47.2 መተማ 52.4 ሞጣ 45.8 ማይጸምሪ 55.3 43.4 ነቀምቴ 78.2 33.1 ፓዌ 47.0 40.1 33.8 ሶዶ 41.2 ሲርባአባያ 44.4 38.6 35.8 አማን 69.0 ቋራ 48.4 ሶጊ 71.2 በሚ.ሜትር ይገኙበታል።


በአጠቃላይ ባለፉት አሥቀናት በአማራ፣ በአብዛኛውትግራይ፣ በአብዛኛውኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሰሜናዊና ምዕራባዊ ክፍል፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ አብዛኛው ዞኖች፣ ከ50-206 የሚደርስ ዝናብ ከ6-10 ቀናት ያህል የነበራቸው ሲሆን፤ የሰሜን ወሎ ዞን፣ የአርሲና የባሌ ዞኖች፣ የቦረናና የጊጂ ዞኖች፣ የሰገን ህዝቦች፣ የደቡብ ኦሞ፣ ጋምቤላ፣ሐረር፣ ድሬዳዋ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ምዕራብ ሸዋ፣አዲስ አበባ ከ5-50 ሚ.ሜትር የደረሰ ዝናብ ከ2-5 ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2)።

ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር የምዕራብና የመካከለኛው ትግራይ፣ ከአማራ ከዋግ ህምራ፣ከአፋር ዞን 2 እና 4፣ ከምዕራብ ወለጋ ምዕራባዊው ዳርቻ እንዲሁም ከደቡባዊው የቦረና ዞን በስተቀር ሁሉም ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው። የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ዝናብ አግኝተዋል(ካርታ 3)


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት



**ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር**





በወቅቱ ዝናብ የማያገኙ አካባቢዎች | ከመደበኛ በታች | መደበኛ | ከመደበኛ በላይ

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው የጁላይ የመጀመሪያው አስር ቀናት የወቅቱ የክረምት ዝናብ በአብዛኛው በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የቀጠለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ አከባቢዎች ጥሩ የአፈር እርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በወቅቱ ለሚከናወኑ የመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ በተለይም፣ ለዘር መዝራት፣ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ በተጨማሪም ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አከባቢዎች ለመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ለግጦሽ ሳር ልምላሜ የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የተገኘው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በተወሰነ መልኩ በግብርናው ሥራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በጁላይ የመጀመሪያዉ አስር ቀናት አጋማሽ ላይ በጎንደርና በአዘዞ አካባቢ በነበረዉ ከባድ ዝናብ ምክንያት ወንዝ ከመጠን በላይ ሞልቶ በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ





## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ጁላይ 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ አብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት ሁኔታ ላይ እንደነበሩ መረጃችን ያመለክታል፡፡ በዚሁ መሠረት የአባይና ተከዜ፣ ጥቂት የላኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ የስምጥ ሸለቆ እና አብዛኛው የአዋሽ ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን  አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል የላኛውና የታችኛው ገናሌዳዋ እንዲሁም የላይኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ከከፊል ደረቅ አስከ መጠነኛ እርጥበት ያገኙ ሲሆን የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች  ደረቃማ ሁኔታ ላይ ነበሩ (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1-10/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን




## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በይበልጥ እየተጠናከሩ በመሄድ ከቀዳሚው አሥር ቀናት በተሻለ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን በመሸፈን እርጥበታማ አየር ይዘወተርባቸዋል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ አዲስ አበባ፤ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የሰሜን ሸዋ በተጨማሪም የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ሁሉም የትግራይ ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋና የቤንች ማጂ፣ የጉራጌ፣ የሀዲያ፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋና የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት መንስኤ ሊሆን ይችላል። ከዚህም ሌላ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ የአፋር ዞን 3 እና 5 እንዲሁም የአርሲና ባሌ ዞኖች፣ የሰገን ህዝቦች እንዲሁም የጅጅጋና የሽንሌ ዞኖች አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከሚኖራቸው በስተቀር በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ፡፡

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሁለተኛዉ አስር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች የመኸር ስራ አንቅስቃሴ በስፋት የሚከናወን ሲሆን፣ በተለይም የክረምቱ ዝናብ በአንፃራዊ መልኩ ዘግይቶ በሚጀምርባቸው የሰሜንና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ማሳ የሚዘጋጅበትና የተለያዩ የመኸር ሰብሎች የሚዘራበት ጊዜ ነዉ፡፡

ከላይ በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በሚቀጥሉት የጁላይ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የመኸር እርሻ እንቅስቃሴ በሚያከናውኑ አካባቢዎች እርጥበታማ ሁኔታው

እንደሚጠናከር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል በትንበያው ተመልክቷል፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበታማ ሁኔታ በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት ከማሟላት አንጻር አወንታዊ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች በጁላይ ሁለተኛዉ አስር ቀናት ለሚዘሩ የመካከለኛ ጊዜ የመኸር ሰብሎች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በተለይም በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው እርጥበታማ ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻልም አልፎ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ሚና የሚኖረው ሲሆን የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማጠራቀም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ከቅፅበታዊ ጎርፍ ጋርተያይዞ በተለይም ለጎርፍና ለመሬት መንሸራተት ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ጥንቃቄ ሊያደርጉ የሚገባ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ ነባር የውሀ መፋሰሻ ቦዮችን ከማጽዳት ጎን ለጎን የጎርፍ መቀልበሻዎችን አስቀድመው እንዲያዘጋጁ ይመከራሉ፡፡ እንዲሁም በወንዝ አካባቢ የሚገኙ የሰብል ማሳዎች ከወንዝ መሙላት ጋር ተያይዞ በሚፈጠር የውሃ መጠለቅለቅ እንዳይዋጡ የመከላከያ ተግባራትን ቀደም ብሎ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ የእርጥበት መብዛት የሚያጠቃቸውና ውሀ የመያዝ አቅማቸው ዝቅተኛ ሆነ የአፈር ይዘት ያላቸው አካባቢዎች ውሀ በቀላሉ ማሳ ላይ ሊተኛና በሰብሎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል ይህንኑ ለመከላከል የሚያስችሉ ተግባራት አስቀድመው ማከናወን ይገባቸዋል፡፡ ከሰብል ጥበቃ አንፃርም ከእርጥበት መብዛት ጋር በተያያዘ ሊከሰቱ የሚችሉ የሰብል በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአንፃሩ ደረቃማ ሊሆኑ እንደሚችሉ የተጠቀሱት አካባቢዎች ሊያገኙ የሚችሉትን መጠነኛ እርጥበት ከብክነት የመከላከል ተግባራትን ማከናወን ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ጁላይ 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስርት ቀናት ማለትም እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2018 ውስጥ በአብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶች የተሻለ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃችን ያመለክታል፡፡

በመሆኑም በሚቀጥሉት አስርት ቀናት ውስጥ በውሃው ዘርፍ እንቅስሴው ላይ ሊኖር የሚችለውን ተፅዕኖ ስንመለከት በአብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶች እርጥበታማ ሁኔታ ላይ ይቆያሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያዞ የተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ አባይ የላኛውና መካከለኛው አፋር

ደናክል፣ የስምጥሸለቆ፣ የኦሞ ጊቤ፣ የላይኛው ገናሌ ዳዋና የዋቢሸበሌ እንዲሁም አብዛኛው የአዋሽ ተፋሰሾች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ ሊያገኙ የሚችሉ ሲሆን፤ በአንዳንድ በተለይም በከፍተኛ ቦታዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ጥቂት የታችኛው  የስምጥ ሸለቆና ኦሞ ጊቤ፣ መካከለኛው  የገናሌ ዳዋ፣ የዋቢሸበሌ፣ የአዋሽ እንዲሁም ጥቂት የላይኛው የኦጋዴን ተፋሰሶች መጠነኛ ዝናብ ሊያገኙ የሚችሉ ሲሆን የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቃማ ሆነው ይቆያሉ፡፡በተጨማሪም መደበኛና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን በሚያገኙ ተፋሰሶች ላይ በተለይ በከፍተኛ ቦታዎች ላይ ጎርፍና የመሬት መንሸራተት ሊከሰት ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡፡ እንዲሁም ከፍተኛ በታዎች ላይ የሚዘንበው ዝናብ በዝቅተኛ ቦታዎች ላይ  ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ይችላል። በተለይም ረባዳማና ወንዞች አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ እንዳይጎዳ የሚመለከታቸው አካላት ቅድመ ጥንቃቄ በማድረግ በሰውና በእንስሳት ላይ አደጋ እንዳያደርስ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው እናሳስባለን፡፡